**በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣**

**ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ**




# ከሴፕቴምበር 11-20፣ የነበረው የአየር ሁኔታ እና ከሴፕቴምበር 21-30፣ ከኦክቶበር 1-10/2026 የሚኖረዉ የአየር ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ሴፕቴምበር 2026

አዲስ አበባ

## 1. እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ

ባለፉት አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ሰሜን፣ መካከለኛዉ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተሻለ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ በመካከለኛዉ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በ34 የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ የሆነ ከባድ መጠን ያለዉ የዝናብ መጠን ነበራቸዉ (ምስል 1) ፡፡

በተጨማሪም በምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብና ሰሜን መስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሰዓት ዉስጥ 40-75.4 ሚ.ሜ የሚደርስ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ከተመዘገበባቸው የሀገሪቱ አከባቢዎች መካከል ኤጀሬ 43.5፣ ዳሊፋጊ 63፣ ደብረ ማርቆስ 68.8፣ ገምቢ 56.9፣ ጎብየሬ 44.3፣ ጉጉፍቱ 48.6፣ ካቺሴ 50፣ ኩሉቢ 47.6፣ ሊሙገነት 40.5፣ ማንኩሽ 75.4፣ ማሻ 40.2፣ መተማ 47.2፣ ሞጣ 45.6፣ ሻምቡ 44.5፣ ሽሬ 58.5 ይገኙበታል ፡፡




ምስል1:ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 በ24 ሰዓት ውስጥ ከ40 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ የተመዘገበባቸው

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብ፣ መካከለኛዉ፣ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ሸካ፣ ቤንች ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳዉሮ ዞኖች፤ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ሀዲያ፣ የም፣ ስልጤ፣ ሃላባ፣ ከምባታ ዞኖች፣ ከደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ወላይታ፣ አዲስ አበባ ላይ ከ31-140 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ3-10 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር፤ ከኦሮሚያ ክልል ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ሁሉም የሸዋ ዞኖች፣ ሸገር ከተማ፣ ከአማራ ክልል የሰሜን፣ ምዕራብ፣ መካከለኛዉና ደቡብ ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ ምዕራብና ምስራቅ ጎጃም፣ አዊ፣ የደቡብ እና የሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ዞኖች፣ ከትግራይ ክልል የምዕራብ፣ የሰሜን ምዕራብና ደቡብ ትግራይ ዞኖች፣ ከአፋር ክልል ሁሉም ዞኖች፣ ከቤንሻንጉል ጉምዝ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ልዩ ወረዳ፣ ከጋምቤላ ክልል አኝዋክ፣ መዠንግ፣ ኑዌር እና ኢታንግ ልዩ ወረዳ፤ አዲስ አበባ በአብዛኛ መደበኛ እና በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ ከመደበኛ በላይ የሆነ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት




ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ በተለይም ምዕራብ አጋማሽ፣ መካከለኛውና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ ይህም የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ቀደም ሲል ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃና ፍሬ በመሙላት ላይ ለሚኙት እንደ ማሽላና በቆሎ ለመሳሰሉት የረጅም ጊዜ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች፣ ለፍራፍሬዎችና ለጓሮ አትክልቶች የውሃ ፍላጎታቸውን ከማሟላት አንጻር ከፍተኛ ጠቀሜታ ነበረው፡፡ በተጨማሪም የክረምት ወቅታቸውን ጠብቀው ተዘርተው ፍሬ በማፍራትና በማበብ ላይ ባሉት የመካከለኛና የአጭር ጊዜ ሰብሎች እንዲሁም በወቅቱ መጨረሻ ለሚዘሩ የጥራጥሬ ሰብሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት ምቹ ሁኔታን ከመፍጠሩም በላይ በሰሜን ምስራቅና በምስራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት ጠቀሜታው የጎላ ነበር። በሌላ በኩል በአንዳንድ የደቡብ የሀገሪቱ ስፍራዎች እየተስፋፋ ያለው እርጥበት በአካባቢው ለሚካሄደው የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ ከመኖሩም በላይ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት አዎንታዊ ጎን ነበረው (ካርታ 4)።

## 1.3 እ.ኤ.አ ከኦገስት ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባለፉት ቀናት በአብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ አዋሽ፣ አፋር ደናክል፣ ተከዜ፣ ላይኛውና መካከለኛ፣ ዋቤ ሸበሌ እንዲሁም ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ በጣም ከፍተኛ የሆነ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ነበራቸው። እንዲሁም አይሻና ላይኛውና ጥቂት ኦጋዴን ከመጠነኛ እስከ እርጥበታማ የገፀ ምድር ውኃ ፍሰት ነበራቸው። በኩል በአብዛኛው የኦጋዴን፣ የመካከለኛና የታችኛው ዋቤ ሸበሌ፣ የገናሌ ዳዋ፣ የስምጥ ሸለቆ እንዲሁም በጥቂት ላይኛው ተከዜ ተፋሰሶች በደረቅ አየር ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 5)።




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 11 እስከ 20/2026 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2.እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በሴፕቴምበር የመጨረሻዎቹ አስር ቀናት ለክረምት ዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ደቡብ ምዕራብ፤ ምዕራብ፤ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛው የሀገሪቱ አከባቢዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡ ይሁን እንጂ በምስራቅና እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ ከባቢዎች ላይ እየቀነሱ ይሄዳሉ (ካርታ 6)። ስለሆነም እርጥበታማው የአየር ሁኔታ በተለይም በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ በመጠንም ሆነ በሥርጭት እየተስፋፋ ከመሄዱ ጋር ተያይዞ በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራቸዋል፡፡ በተጨማሪም በምስራቅ እና ሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ያመላክታሉ (ካርታ 6)፡ ፡ በተጨማሪም በደቡብ ምዕራብ እና ምዕራብ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የአየር ሁኔታ ክስተቶች ላይ በመነሳት ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖር የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናቶች ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት የክረምት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑ የሀገሪቱ አከባቢዎች ብዙ ቦታዎቻቸውን የሚሸፍን ከቀላል እስከ መካከለኛ (ከ1-29 ሚ.ሜ) መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በተጨማሪም በውሃ አካላትና በከባቢ አየር ውስጥ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በመካከለኛው፣ ደቡብ ምዕራብ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በ24 ሠዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚያገኙ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች




ካርታ 6 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21-30/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| ክልል | ዞን | በ 24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን |
|---|---|---|
| ኦሮሚያ | ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ እና አብዛኞቹ የሸዋ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ በላይ) |
| | ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ እና ምዕራብ ጉጂ ዞን | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ የባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ የአዊ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| | ዋግህምራ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ የሰሜን ሸዋ ዞኖች እና የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፤ | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ጋምቤላ | አኝዋክ እና መዥንግ ዞኖች | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ቤንሻንጉል ጉምዝ | ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ዞኖች | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ | ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |
| ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ ማረቆ ልዩ ወረዳ | ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ) |
| አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ እና ሐረሪ | | ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ትግራይ | የምዕራብ እና የሰሜን ምዕራብ ዞኖች | ከቀላል እስከ ከባድ መጠን (ከ11 እስከ 30 ሚ.ሜ) |

| | | |
|---|---|---|
| | መካከለኛው፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ ክልል | ሁሉም የክልሉ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ ከባድ መጠን (ከ1-30 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ እና ኮንሶ ዞኖች | ከቀላል መጠን እስከ መካከለኛ መጠን (ከ1-29 ሚ.ሜ) |
| ሶማሌ | ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ቀላል መጠን (ከ1-11 ሚ.ሜ) |

## 2.1 እ.ኤ.አ ከኦክቶበር 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ

በመደበኛ ሁኔታ በኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት የክረምት ድንበር (ITCZ) ወደ ደቡብ አቅጣጫ ከሚያደርገው እንቅስቃሴ ጋር ተያይዞ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በደቡብ የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ እየተጠናከሩ ይሄዳሉ፡፡ ስለሆነም የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያ በተጠናከረ ሁኔታ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸውን የሚያገኙ ሲሆን፣ በተመሳሳይ ሁኔታም በምዕራብ እና በደቡብ ምዕራብ ዝናቡ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡

በመጪዎቹ የኦክቶበር የመጀመሪያዉ አሥር ቀናት አሁን ከሚታዩትና በቀጣይነትም ከተተነበዩት የትንበያ መረጃዎች እንደሚያሳዩት ዝናብ ሰጭ የአየር ሁኔታ ክስተቶች በደቡብ፣ በምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ ገጽታ ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የጉጂ፣ ምስራቅ ጉጂ፣ ምስራቅ ቦረና ዞኖች፤ የሲዳማ ክልል ዞኖች፤ የሶማሌ ክልል ደቡባዊ ዞኖች እና የደቡብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም ቀደም ብሎ የክረምት ወቅት ዝናብ ሲያገኙ የነበሩ የምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ፣ እንዲሁም ምስራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ቀጣይነት ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም በፀሃይ ሀይል ታግዞ ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች ላይ በመነሳት በምዕራብ፣ በመካከለኛው እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት በ24 ሰዓት ውስጥ ከ30 ሚ.ሜ በላይ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ይኖረቸዋል፡፡

## 2.2 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት ቀናት በምዕራብ፣ ሰሜን ምዕራብ፣ ደቡብ ምዕራብ እና መካከለኛዉ የሀገራችን አካባቢዎች በብዙ ቦታዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው የአፈር ውስጥ እርጥበት እንደሚኖር ይጠበቃል። በተጨማሪም በሰሜን ምስራቅ እና ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው የአፈር ዉስጥ እርጥበት ያገኛሉ። በመሆኑም የሚኖሩ መልካም አጋጣሚዎችን በአግባቡ ለመጠቀምና አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ለመቀነስ የሚያስችል ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳብ ከወዲሁ ተግባራዊ እንዲያደርጉ ከታች የቀረቡትን ዝርዝር ተግባራት ማከናወን ያስፈልጋል፡፡ ሠንጠረዥ ይምልከቱ 2፡፡

## 2.3 እ.ኤ.አ ከሴፕቴምበር 21 እስከ 30/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስር ቀናት የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት ተፋሰሶች ላይ ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን የሚደረስ የገፀ ምድር የውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል። በመሆኑም የሚመለከታቸው የዘርፉ አካላት የሚኖሩ መልካም ዕድሎችን በአግባቡ ለመጠቀምና ተያያዥ ስጋቶችን ለመቀነስ የሚከተሉትን ተፋሰስ ተኮር የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ኢንስቲትዩቱ ይጠቁማል። ሠንጠረዥ ይምልከቱ 3፡፡

Ethiopian Meteorology Institute

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የክረምት ዝናብ ተጠቃሚና የመኸር ሰብል አብቃይ እንዲሁም አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች | | | |
|---|---|---|---|
| **ከመካከለኛ እስከ ከባድ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የተሰጠ ምክረ ሃሳብ** |
| ቄለም ወለጋ፣ ምዕራብ ወለጋ፣ ምስራቅ ወለጋ፣ ሆሮ ጉድሩ ወለጋ፣ ኢሉባቦር፣ ቡኖ በደሌ፣ ጅማ፣ ምዕራብ አርሲ፣ አርሲ፣ ሸገር ሲቲ ፣ አብዛኞቹ የሸዋ ዞኖች ፣ የምዕራብ፣ መካከለኛ፣ ደቡብ እና ሰሜን ጎንደር፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ የሰሜን፣ የምዕራብ እና የምስራቅ ጎጃም፣ አዊ ፣ ካማሺ፣ መተከል፣ አሶሳ፣ ማኦ ኮሞ ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ምዕራብ ኦሞ ዞኖች ፡ ፡ | ➢ የአፈር ውስጥ እርጥበት መሻሻል<br>➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ ዘግይተው ተዘርተው በተለያየ የዕድገት ደረጃ ላይ ላሉ ሰብሎች እድገት<br>➢ ለእንስሳት መኖና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ የውሃ ማጠራቀሚያዎችን ለማጎልበት<br>➢ ለቋሚ ተክሎች እድገት እና ለግጦሽ ሳር ዕድገት ለአረንጓዴ አፅዋት ልምላሜ | ➢ ተዳፋታማ በሆኑ አካባቢዎች የውኃ በሰብሎች ላይ መተኛት<br>➢ የአረም መስፋፋት<br>➢ የሰብል በሽታና ተባይ መከሰት | ➢ ተዳፋታማ ማሳዎች ላይ የተዘጉ የማፋሰሻና የማንጣፈፊያ ቦዮችን ማስተካከል<br>➢ የሰብል በሽታንና አረምን አስቀድሞ መከላከል፤<br>➢ እርጥበት አጠር አካባቢዎች የዝናብ ውሃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>➢ አርሶ አደሮች የማሳ ጉብኝት በየጊዜው ማድረግ<br>➢ የድጋሜ አረምን ማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |

| ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ እርጥበት የሚያገኙ ዞኖች | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| ምስራቅ እና ምዕራብ ሐረርጌ፣ ባሌ ፣ ምዕራብ ጉጂ ፣ ዋግህምራ፣ ደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ ሰሜን ሸዋ ፣ የኦሮሞ ብሄረሰብ ልዩ ዞን፣ አኝዋክ ፣ መዥንግ ፣ጉራጌ፣ ምስራቅ ጉራጌ፣ ስልጤ፣ ሀዲያ፣ ከምባታ፣ ሀላባ፣ የም፣ ጠምባሮ ልዩ ወረዳ፣ ቀቤና ልዩ ወረዳ፣ማረቆ ልዩ ወረዳ፣ አዲስ አበባ፤ ድሬዳዋ ፣ ሐረሪ ፣ ምዕራብ እና ሰሜን ምዕራብ ትግራይ፣ መካከለኛዉ፣ ምስራቅ፣ ደቡብ ምስራቅ እና ደቡብ ትግራይ ዞኖች ፣ የሲዳማ ሁሉም የክልሉ ዞኖች፣ ወላይታ፣ ጋሞ፣ ጎፋ፣ ጌድዮ፣ ኮሬ፣ ባስኬቶ ፣ ኮንሶ ፣ ሲቲ እና ፋፈን ዞኖች | ➢ ለረጅምና መካከለኛ ጊዜ ሰብሎች እድገት እና ፍሬ ለማፍራት<br>➢ የአረንጓዴ እፅዋት ልምላሜ፣ ለመጠጥ ውሃና ለግጦሽ ሣር አቅርቦት መሻሻል<br>➢ የዝናብ ውሃን ለማሰባሰብና ለማጠራቀም | ➢ የትነት መጠን መጨመር፤<br>➢ የፀረ ሰብል ተባይ መከሰት ፤<br>➢ በተወሰኑ ቦታዎች ላይ የአፈር ውስጥ እርጥበት ዝቅተኛ መሆንና<br>➢ ለሰብሎች የውሃ ፍላጎት በቂ አለመሆን | ➢ የሚገኘዉን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም<br>➢ የዝናብ ውኃን በማሰባሰብ በደረቅ ሰሞናት ተግባር ላይ ማዋል<br>➢ የአፈር ውስጥ የትነት መጠንን ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን ማከናወን፤<br>➢ ለእንስሳት የግጦሽ ሣርን በአግባቡ መጠቀምና መጠበቅ፤<br>➢ ፀረ-አረምና ፀረ ተባይ ኬሚካሎችን ከግብርና ባለሙያ ጋር በመመካከር መተግበር |

ሠንጠረዥ 3 በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| ከመካከለኛ እስከ ከፍተኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|
| • በላይኛው ባሮ አኮቦ፣ በታችኛው አባይ፣ | • የገፀ-ምድር ውሃ መጨመር<br>• የከርሰ-ምድር ውሃ ማደግ<br>• የግድቦች ክምችት ማደግ<br>• የመጠጥ ውሃ ተደራሽነት መጨመር | • የደለል ክምችት ስጋት መጨመር | • የዝናብ ውሃን በማሰባሰብ ለተለያዩ ፍጆታዎች ይጠቀሙ<br>• የመጠጥ ውሃን አክመውና አጣርተው ይጠቀሙ<br>• የውሃ ማፋሰሻና መስመር ቦዮችን በጥንቃቄ ያፅዱ |
| **ከቀላል እስከ መካከለኛ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| • በአብዝኛው አባይ፣ ተከዜ፣ ላይኛው አዋሽና ገናሌ ዳዋ | • የውሃ ፍሰት፡- መሻሻል<br>• የጎርፍ ስጋት፡- መቀነስ<br>• የከርሰ-ምድር ውሃ፡- ማደግ<br>• የአፈር እርጥበት፡- መጨመር | • ከፍተኛ ትነት<br>• የአፈር እርጥበት መቀነስ | • የሚገኘውን የዝናብ ውኃ አክሞ መጠቀም<br>• ወራጅ የዝናብ ውኃን ማሰባሰብና ማጠራቀም<br>• ከቤት ጣራ ላይ ውኃ የማሰባባሰብ ማጠራቀም<br>• የአየር ሁኔታ መረጃን በቅርበት መከላከል |
| **ደረቅ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት** | **አዎንታዊ ተጽዕኖ** | **አሉታዊ ተጽዕኖ** | **የውሃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ** |
| • ዋቢ ሸበሌ፣ዋቤ ሸበሌ፣ አፋር ደናክል፣ መረብ ጋሽ፣ ኦጋዴን፣ አይሻ፣ ታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ገናሌ ዳዋና ኦሞ ጊቤ፣ | • የጎርፍ ሆነ የደለል ስጋት አለመኖር፣ | የገጸ ምድር ትነት መጠን መጨመር | • የውሃ እጥረት ባለባቸው አካባቢዎች ተደራሽነትን ማረጋገጥ<br>• የሚገኘውን ውሃ በውጤታማነት ማስተዳደር<br>• የገፀ-ምድር ውሃን በአግባቡ መጠቀም<br>• የዝናብ ውሃን ለተለያዩ ፍጆታዎች ማዋል<br>• የአየር ንብረት ትንበያዎችን መከታተል |